DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS




www.dcps.dc.gov

ጥያቄዎች አሉዎት? በቀጣዩ አድራሻ ያግኙን
(202) 719-6613 ወይም ofpe.info@dc.gov.

1200 First Street, NE, Washington, DC 20002

/dcpublicschools @dcpublicschools @dcpublicschools

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ



# የክፍል ደረጃ 5



# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ የአጠቃቀም መንገድ፣

ይህ መምሪያ ልጅዎን በቤት ውስጥ ለማገዝ የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ይሰጥዎታል። በዚህ የመረጃ ጥራዝ ውስጥ፣ ልጅዎ የትምህርት ግቦቹን እንዲያሳካ ለማገዝ እንዲችሉ በ DCPS ስርዓተ ትምህርት ላይ የተመሰረቱ ስትራቴጂዎችን ያገኛሉ። ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ የሚማረውን ትምህርት እና በተጨማሪም በቤት ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ ይጨብጣሉ/ያገኛሉ።

## እርስዎ ማድረግ የሚችሉት፣

በልጅዎ አካዳሚክ ብቃት ላይ እርስዎ ወሳኝ ሚና ይጫዎታሉ። በቤት ውስጥ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ እነዚህ የተወሰኑ አስፈላጊ ነጥቦች ናቸው፡

- ትምህርት የስኬት መሰረት መሆኑን ልጅዎ እንዲያውቅ ያድርጉ።
- ልጅዎ 5ኛ ክፍል ውስጥ ምን ይማራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ይወቁ።
- ልጅዎ ከፍተኛ የሆኑ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ አካዳሚያዊ ግቦችን እንዲያሰቀምጭ ያግዙት።
- የቤት ስራ በተገቢው ሰአት እና በአግባቡ እንዲያጠናቅቅ በቂ ጊዜ ይስጡ።
- በት/ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ሒደታዊ ለውጦችን ያለማቋረጥ ይከታተሉ።
- ለልጅዎ ይሟገቱ።
- የልጅዎን ጥንካሬ ከመምህሩ ጋር ይጋሩ።

## የልጅዎን መምህር መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፣

ከልጅዎ መምህር ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ስለ ልጅዎ የትምህርት አቀባል እና ሁኔታ ላይ ትኩረት እያደረጉ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡

- የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? የመማር ግብ አስመልክቶ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች እንደ ምሳሌ ሊነግሩኝ ይችላሉ?
- የልጄን ስራ እንደ ምሳሌ ማየት እችላለሁ? እነዚህን የመማር ግቦች የሚያሳካው ወይም የማያሳካው እንዴት ነው?
- ልጄ በትምህርቱ እያለ/ ከሆነ ደረጃ በላይ ሲዘልቅ ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ የሚገባኝ ምንድናቸው? ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላሁ?
- ቤት ውስጥም መተግበር ያለባቸው የመማሪያ ክፍል ውስጥ መደበኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- የእርስዎን ክፍለ ጊዜ በተመለከተ ለልጄ በየቀኑ ማቅረብ ያለብኝ ጥያቄዎች ምን ዓይነት ናቸው?

## ከልጅዎ ጋር መነጋገር፣

ጥሩ ጭውውቶች ልጆቻችነ በሕይወታቸው ውስጥ እኛ እንደሚያገባን እንዲያዩ ያግዛሉ። እነዚህ ከልጆችዎ ጋር መልካም ውይይት በሚያደርጉበት ጊዜ በቅድሚያ መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፡

- እስኪ በቀንህ ውስጥ ምርጥ ስለምትለው ጊዜ አውራኝ።
- በውሎህ ውስጥ ያጋጠመህ እጅግ በጣም ፈታኝ ነገር ምንድነው?
- ዛሬ ከተማራችሁት ውስጥ አንድ ነገር ልታሳየኝ ትችላለህ?
- ት/ቤት ውስጥ የምታነቡት መፅሐፍ ምንድን ነው? የምትወደውን መገለጫ ባህርይ ብትነግረኝ? ይህን መገለጫ ባህርይ የምትወደው ለምንድን ነው?
- በት/ቤት ውስጥ ከዚህ በላይ መስራት አለብኝ የምትላቸው ነገሮች ምንድናቸው? በአነስተኛ መጠን ማድረግ አለብኝ ብለህ የምታስበውስ ምንድን ነው? ለምን?

# የአምስተኛ ክፍል ተማሪዬ እየተማረ ያለው ነገር

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| የበልግ ወቅት | ተማሪዎች አሜሪካ ወደ ምዕራብ ያደረገችውን መስፋፋት እና የመጀመሪያዎቹ አሜሪካውያንና አውሮፓውያን በመሳሰሉ የተለያዩ ሰዎች ላይ ስላሳደረው ተጽእኖ ይማራሉ። ወደ ምዕራብ ጉዞ የተደረገበትን ገፊ ምክንያትም ይዳስሳሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ስለ የእርስ በእርስ ጦርነቱ እና በቀጣይነት ስለነበረው የመልሶ ግንባታ ዘመን ይማራሉ። የእርስ በእርስ ጦርነቱ በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ ይተነትናሉ፤ ሃገሪቱ በዚህ ጊዜ ለምን እንደተከፋፈለች፣ የተለያዩ የግጭቶችን መልክ እንዴት ማንበብ እንደሚቻልና የሚያቅፏቸውን አተያዮች እንዴት ማነጻጸር እንደሚቻል። | ተማሪዎች የዴሲማል ቁጥሮችን ወደ ሺህ ቤት ለማወዳደር፣ ቅደም ተከተል ለማስያዝ፣ ለመደመርና ለመቀነስ የቦታ ዋጋን ይገነዘባሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ቅንፎችን በመጠቀም ቀላል አገላለጾችን መጻፍና መፍታት ይችላሉ። ተማሪዎች ባለ ብዙ አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን ያባዛሉ፣ ያካፍላሉ። | ተማሪዎች በሕዋ ላይ ያሉ ነገሮች እንዴት እንደሚታዩና እርስ በርስ እንዴት እንደሚገናኙ ይመረምራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ስነ ነገሮች ጸባያትና ከሌላ ነገር ጋር ስላላቸው ተግባቦት ይዳስሳሉ። | ሒደታዊ ዕድገት ምንድን ነው? ተማሪዎች በዩኤስ ውስጥ ያሉ መልክዓ ምድራዊ ክልሎችን በመለየት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የነበሩ ሰፋሪዎች ከ 1780ዎቹ እስከ 1850ዎቹ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ያደረጉት እንቅስቃሴ አውድ እና መንስኤዎችን ይተነትናሉ።<br>•••<br>መልሶ ግንባታ በሒደት ላይ ያለ ስራ ነው? ተማሪዎች የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት ዲሲን እንዴት እንደቀየራትና በእርስ በርስ ጦርነትና በመልሶ ግንባታ ወቅት ግጭት ያስከተሉትን ሁኔታዎች ይመረምራሉ። |
| የክረምት ወቅት | ተማሪዎች ስለ ሶላር ሲስተም እና አካላቱ ለመማር የሚከተሉትን ይተነትናሉ፡ የፀሐይ ተጽእኖ እና የቢንግ ባንግ ውጤትና የከዋክብት ክምችቶችና የሶላር ሲስተማችንን እንዴት እንደፈጠረ። ተማሪዎች ቴክኖሎጂና ጽሑፎችን በመጠቀም በማስረጃ ላይ የተመሰረተ፣ በእውነታዎችና ዝርዝሮች ላይ የተመሰረተ መረጃ ሰጪ ጽሑፍ እንዴት እንደሚጽፉ ይማራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች አዳዲስ የፈጠራ ስራዎችን በማጎልበት፣ የፈጠራ አሳቢዎች፣ ፈጣሪዎችና ሳይንቲስቶች ለህብረተሰቡ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በተመለከተ አዳዲስ ነገሮችን ስለ መፍጠር ሒደት ግንዛቤ ያሳድጋሉ። ተማሪዎች አዳዲስ ነገር ፈጣሪዎች አዳዲስ ነገር ለመፍጠር ያስቻላቸውን ዋነኛ ማስረጃ ከሕይወታቸው ውስጥ ይጠቅሳሉ፣ ሁለት አዳዲስ ፈጣሪዎችን ያወዳድራሉ፣ እነደዚሁም መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ይጽፋሉ። | ተማሪዎች ክፍልፋዮችንና የዴሲማል ክፍልፋዮችን ይደምራሉ፣ ይቀንሳሉ፣ ያባዛሉ፣ ያካፍላሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ስለ ይዘት ግንዛቤ በመያዝ ከመደመርና ከመቀነስ ጋር ያዛምዳሉ። | ተማሪዎች በስርዓተ ምህዳር ውስጥ የነገሮችን እና የኢነርጂን ፍሰት ያጠናሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች በምድራችን ላይ ስላለ ውሃ እና የመሬትን ተፈጥሯዊ ሐብቶችና አካባቢዎች ጥበቃን በተመለከተ ይማራሉ። | በዓለም ዙሪያ ከመጠን ያለፈ ጣልቃ ገብነት መፈጸም ዩናይትድ ስቴትስን በሃገር ውስጥ ይጎዳታል? በሚድያ እና በአሜሪካውያን መካከል የነበረው ግንኙነት መለወጡ ዩናይትድ ስቴትስ በአለም አቀፍ ጦርነቶች ውስጥ እንድትሳተፍ እንዴት አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይመረምራሉ።<br>•••<br>ለውጥን ለማጎልበት የተሻለው መንገድ ምንድን ነው? ተማሪዎች ለታላቁ ፍልሰት፣ ለሐርለም ሕዳሴና ለሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ ያደረጉ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ። |
| የፀደይ ወቅት | ተማሪዎች ስለ አሜሪካውያን የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ እየተማሩ የሲቪል መብቶች አራማጆችን ተሞክሮ፣ የእነርሱ እርምጃዎች የሰዎችን እምነት፣ አመለካከትና አተያይ እንዴት እንቀየሩና ፈታኝ ለነበሩ ሁኔታዎች እንዴት ምላሽ እንደሰጡ ያጠናሉ። ገጸ ባሕርያትን እንዴት እንደሚመረምሩ ይማራሉ፣ ገጸ ባሕርያትንና ክስተቶችን ያስተሳስራሉ፣ መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ይጽፋሉ። | ተማሪዎች በኮርዲኔት ፕሌን መልመጃዎችን ይፈታሉ። | | |

# ከአምስተኛ ክፍል ተማሪዬ ጋር የምለማመዳቸው ተግባራት

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## በየቀኑ ለ20 ደቂቃ ያህል አብረራችሁ አንብቡ።

### የበልግ ወቅት

ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ጉዞ ባደረጉበት ወቅት ያልነበሩ አምስት ዘመናዊ አስደሳች ነገሮችን ይዘርዝሩ። አሁን ወደ ምዕራብ መጓዝ የተለየ የሚሆነው ለምንድን ነው? ዘመናዊ ሕይወት ይበልጥ ቀላል ወይም ይበልጥ አስቸጋሪ ነው?

•••

በሕይወታችሁ ውስጥ ጦርነት እና ግጭት በሰዎች ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ እንዳሳደሩ ተወያዩ። አገልግሎታቸውን የሰጡንን የምናከብረው እንዴት ነው? ወደ bit.ly/WriteOurTroops በመግባት ለወታደሮቻችን ወይም ለቀድሞ ወታደሮች ደብዳቤ (ወይም ኢሜይል) ይላኩ።

ከልጅዎ ጋር በልኬት ኦሎምፒክ ውስጥ ይወዳደሩ። የተወረወረ ኳስን ርቀት ወይም በውድድር ላይ ያለን ፍጥነት ለከተው ልጅዎ ርቱንና ሰዓቱን ቅደም ተከተል እንዲያሲዝና እንዲያነጻጽር ያድረጉ።

•••

ልጅዎ በተለያዩ የግብይት ጉዞዎች ላይ ልጅዎ ሒሳብ እንዲያሰላ ያድረጉ።

ስለ አልበርት አንስታይን ልጅዎን ያስጎብኙ ፕላኔታሪዩም ስሚዝሶኒያ ብሄራዊ አየር እና የህዋ ሙዚየሞች ያስጎብኙ፡፡

•••

ውሃ፣ ዘይት እና ደስተኛ ታብሌት በመጠቀም የላቫ አምፑል ያዘጋጁ። ይህ መፍትሔ መሆን አለመሆኑን ክፍል ውስጥ በተማሩት መሰረት እንዲነግርዎት ልጅዎን ይጠይቁ።

ልጅዎ በራሱ ማህበረሰብ ውስጥ መሻሻል የተደረገባቸውን መስኮች እንዲለይና እንዲያስረዳ ይጠይቁ።

•••

ልጅዎ የቤተሰብ አባላት በተሰበሰቡበት ቀርቦ ለ Ford’s Oratory Festival ንግግር ለማድረግ እንዲለማመድ ያድርጉ። የአፍሪካ አሜሪካውያን የእርስ በእርስ ጦርነት ሙዚዬም ይጎብኙ (በነጻ)።

በእያንዳንዱ ቀን በንባብ ላይ ምን ያህል ጊዜ እንዳሳለፉ መመዝገቢያ ያዘጋጁ! ከእያንዳንዱ ታሪክ የወደዱትን ገጸ ባሕርይ በመዘርዘር ገጸ ባሕሪው እርስዎ ያደነቁለትን ብቃት ያሳየበትን የታሪኩን ክፍል ይለዩ።

•••

ሶስት አዳዲስ መጻሕፍትን ለማየት በአቅራቢያዎ ያለውን ቤተ መጻሕፍት ይጎብኙ! በአካባቢ የሚገኘውን መጽሀፍት ቤት ቅርንጫፍ ለማግኘት bit.ly/findmylibrary የመረጃ መረባችንን ይጎብኙ፡፡ የሚያነብቧቸውን አዳዲስ መጻሕፍት ወደ ንባብ መዝገብዎ ማከልዎን እርግጠኛ ይሁኑ!

### የክረምት ወቅት

የሰው ልጅ ወደ ጨረቃ የተጓዘ ቢሆንም ወደ ማርስ ግን ገና አልደረሰም። ይህ ማለት ግን አልሞከርንም ማለት አይደለም! ኢንተርኔትን በመጠቀም፣ ወደ ማርስ ለመድረስ የተደረጉ ሙከራዎች ላይ ሁለት የተለያዩ ፕሮጄክቶችን ወይም ኢኒሼቲቮችን ይፈልጉ። ማርስ ላይ እንዳናርፍ የሚከለክሉን ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው? ሳይንቲስቶች እነዚያን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ እየሞከሩ ያሉት እንዴት ነው?

ክፍልፋዮችን ማባዛትና ማካፈልን ይለማመዱ። ከቤትዎ ወይም ከቤተ መጻሕፍት ሆነው የኦንላይን መረጃ ለማግኘት bit.ly/DCPSmultiply ወይም bit.ly/DCPSdivide ይጎብኙ!

U.S. Botanic Gardens በመጎብኘት በርካታ ኤግዚቢቶቻንን እና የተክል ስብስቦችን በነጻ ይመልከቱ። ልጅዎ ማየት የሚችላቸውን የተክልና የእንስሳት ስብስብ ምሳሌዎችን እንዲለይ ይፈትኑት።

ዩናይትድ ስቴትስ በሌሎች ሃገራት ውስጥ ስላላት ተሳትፎ አሁናዊ ጉዳዮች በመወያየት ከዚህ በፊት የነበሩ ክስተቶችን እነዲያነጻጽር ይጠየቁት።

•••

Phillips’ Collection Exhibit of Jacob Lawrence’s Great Migration Series (ነጻ፣ ማክሰኞ - ቅዳሜ፣ አድራሻ 1600 21st Street NW) ይጎብኙ። ለዝርዝር መረጃ Visit phillipscollection.org/visit ይጎብኙ።

ወደ bit.ly/TypingFun በመግባት አዝናኝ ጨዋታዎችና ተግባራትን በመጠቀም በኮምፒዩተር ላይ የመጻፍ ፍጥነትዎን ያሻሽሉ። ሁሉንም ጨዋታዎች ማሸነፍ ይችላሉ?

•••

ዘወትር ማክሰኞ Smithsonian Museum of Natural History’s Butterfly Pavilion በነጻ መጎብኘት ይችላሉ። ጎብኝ። www.mnh.si.edu for information.

### የፀደይ ወቅት

አዲስ ነገር በመፍጠር ሊፈቱት የሚችሉትን ችግር ይለዩ! ሃሳብዎን በመዝገብ ላይ ጽፈው የመረጡትን ሃሳብ በተመለከተ ንድፍ ይሳሉ። ይህን በራሴ መገንባት እችላለሁ ብለው ያስባሉ?

•••

የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ አሁንም ድረስ አግባብነት ያለው ስለመሆኑ የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎች ምንድን ናቸው? በዚህ ርዕስ ላይ ንግግር ይጻፉና ለጓደኞችዎና ቤተሰብዎ ያጋሩ።

በሌጎስ ወይም ሌሎች የኩብ ቅርጽ ያለው ብሎክ አማካይነት አራት ማዕዘን ፕሪዝሞችን በመገንባት መጠንን ይዳስሱ። እያንዳንዱን ብሎክ ሳይቆጥሩ ብሎኮቹን ስለሚቆጥሩባቸው መነገዶች ተወያዩ።

•••

ከልጅዎ ጋር የጦር መርከብ ጌም ይጫወቱ።

ወደ bit.ly/DCPSCherry ገብተው National Cherry Blossom Festival ይጎብኙ።

•••

Visit the Kenilworth Park and Aquatic Gardens’ Water Lily and Lotus festival ይጎብኙ። ለተጨማሪ መረጃ bit.ly/DCPSKen ይጎብኙ።

•••

የበጋ ወቅት ዕቅዶችዎ ምን ምን ናቸው? በበጋው ወቅት መማራሁን ለመቀጠል በጋራ ልትሰሯቸው የምትችሉ አምስት ተግባራት ላይ ጥልቅ የሃሳብ ልውውጥ አድርጉ።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ | የማበልጸጊያ ተግባር